ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ
The Government of National State of Tigray
ቢሮ ልምዓት ሕርሻን ገጠርን
Bureau of Agriculture & Rural Development

ቁጥር/No 294/ሐምም-302
ቀን/Date 3/7/13

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

ለግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ :- <u>በትግራይ ክልል በተፈጠረው ጦርነት የደረሰው ጥቃት</u>

እንደሚታወቀው በትግራይ ክልል በተከሰተው ጦርነት በሰብል፣ በእንስሳትና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራዎች ከፉኛ ጥቃት ኣድርሳል፡፡ የግብርናና ገጠር ልማት ተቅዋማት ደግሞ የወደሙና የተዘረፉ ሲሆኑ በኣጠቃላይ 4.5 ሚልዮን ለረሃብ ተጋላጭ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም ኣርሶ ኣደሩ የሰብልና የእንስሳት ምርቱን፣ ሃብቱኑና ንብረቱን ስለተዘረፈ በቀጣይነት እግሩ የሚተክልበት የግብርና ስራው የሚያስቀጥልበት ችግር ላይ ተጥሏል፡፡

በጦርነቱ ምክንያት በግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ልማት የደረሰው ጥቃት ለመዳሰስና ኣስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ከፌደራልና ከክልሉ ግብርና ባለሞያዎች በጋራ በመሆን በወረዳዎች ዳሰሳና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን የዳሰሳው ግኝት ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ____ ገፅ ሪፖርት የላክን ሲሆን በደረሰው ጥቃት መሰረት ኣስፈልጋውን ድጋፍ እንዲታደርጉልን እንጠይቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

<u>ግልባጭ</u>

- ✓ ለትግራይ ክልል ግዝያዊ መስተዳድር
  <u>መቐለ</u>

# በትግራይ ክልል

# ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ

# በጦርነት ምክንያት የደረሰው

# ጥቃት ኣጭር የዳሰሳ ሪፖርት

የካቲት 2013 ዓ/ም

መቐለ

1. መግቢያ

በትግራይ ክልል የተከሰተውን ቀውስ መነሻ በማድረግ ችግሩን ደረጃ በደረጃ መፍታት እንዲቻል በክልሉ ድጋፍ የሚሰጥ 3ተላለቅ ቡዱኖች በኢያንዳንዳቸው 3-4 ንኡሳን ቡዱኖች ያሉት የባለሙያዎች ቡድን ከክልልና ከፌደራል ባለሞያዎች ተደራጅቶ ወደ 4 ዞኖችና 20 ወረዳዎች ከ 19-30/05/2013 ዓ/ም ለመደገፍ የሞከረ ሲሆን ዝርዝር ሪፖርቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2. ዓላማ

በትግራይ ክልል በተከሰተው ኢፍትሃዊ ጦርነት በሰውና በግብርና ሴክተሩ የደረሰ ጥቃት መዳሰስና መፍትሔሃሳቦችን ማቅረብና መደገፍ

3. የተቀመጡ ግቦች

- በትግራይ ክልል የረሃብና የምግብ ዋስትና ችግር ተጋላጭነትና ጉዳት መዳሰስና ለተጠቂ ህ/ሰብ የእለት እርዳታ እና የልማታዊ ሴፍቲኔት በማመጋገብና በፍጥነት ተደራሽ በሆነ መልኩ ሰብዓዊ ድጋፍ ማድረግ
- በየደረጃው የፈረሱና የተዘረፉ የመንግስታዊ ተቋማት እና የተበተነውን የሰው ሀይል ፈጥኖ መልሶ ማደራጀትና ወደ ስራ ማሰማራት፣

4. ድጋፍ የተደረገላቸው ዞኖች

- በክልሉ ከሚገኙ 6 ዞኖች አምስቱ ዞኖች ማለትም ደቡባዊ፣ ደ/ምብራቅ፣ ምብራቅ፣ ማእከላዊና በከፊል ሰ/መዕራብ ዞኖች ዳሰሳና ድጋፍ የተደረገላቸው ሲሆን የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፣ ምዕራባዊ ዞንና ከደቡባዊ ዞን ደግሞ ራያ ኣላማጣ፣ ኦፍላና ዛታ ገጠር ወረዳዎች ወደ ክልል ኣማራ ገብቷል በሚል ዳሰሳና ድጋፍ ኣልተደረገላቸውም

5. የረሃብና የምግብ ዋስትና ችግር ተጋላጭነትና ጉዳት የሚታደግ የእለት እርዳታ እና የልማታዊ ሴፍቲኔት ሀብት በማመጋገብና በፍጥነት ተደራሽ በሆነ መልኩ ሰብዓዊ ድጋፍ ማድረግ

- በሁሉም ወረዳዎች ህዝብ እንደ ህዝብ በማያቀውና በማያገባው ጉዳይ በሜዳ፣ በቤቱና በማሳው እየተገደለ መሆኑ በተለይም የኤርትራ ሰራዊት በገባቸው ኣከባቢዎች ማለትም ምስራቃዊ፣ ማእከላዊ፣ ሰ/ምዕራብ፣ በኣማራ ልዩ ሃይል ደግሞ

ኣብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ቢሮ ልምዓት ሕርሻን ገጠርን The National Regional State of Tigray Bureau Of Agriculture & Rural Development

ምዕራባዊ ዞን ክፉኛ እየተገደለ መሆኑና አሁንም ወደ ደ/ምስራቅና ደቡባዊ ዞኖች እየተስፋፋ መሆኑ

- በሁሉም ወረዳዎች የህዝብ ሀብትና ንብረት ከማሳው፣ ከቤት እየተወሰደ መሆኑ በተለይም የኤርትራ ሰራዊት በገባቸው አከባቢዎች ማለትም ምስራቃዊ፣ ማእከላዊ፣ ሰ/ምዕራብ፣ በአማራ ልዩ ሃይል ደግሞ ምዕራባዊ ዞን ቤት ያፈራውን በቤት የሚገኙ ቁሳቁሶችና በሮች የተወሰዱ መሆናቸውና አሁንም እየተወሰደ መሆኑ ይህ ተግባር ወደ ደ/ምስራቅና ደቡባዊ ዞኖች እየተስፋፋ መሆኑ

- ጦርነቱ የተከሰተው በሰብል መሰብሰቡ ግዜ በመሆኑ በአብዛኞቹ አከባቢ በትክክል ያልተሰበሰበ መሆኑ

- በደቡብ፣ ደ/ምስራቅና ምስራቅ በከፊል ደግሞ በማእከላይ ዞኖች ያምበጣ ጥቃት የደረሰባቸው በመኖሩ

- በአጠቃላይ በጦርነቱ፣ በወረራውና ባለፈው ክረምት በነበረው ያንበጣ መንጋ ውድመት የትግራይ ህ/ሰብ ከፍተኛ የምግብ እጥረት ተከስቷል
- በርዳትና በልማታዊ ሴፍቲኔትና አፋጣኝ ረድኤት ለማድረስ በየደረጃው ኮሚቴ ከማዋቀር አኳያ በዞን ደረጃ በደቡብና ደ/ምስራቅ በወረዳ ደረጃ ደግሞ በአብዛኞቹ ወረዳዎች ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ስራ የገባ ሲሆን በቀበሌ ደረጃ ከማዋቀር ግን ትልቅ ክፍተት አለው፡፡
- የልማታዊ ሴፍትኔት ተጠቃሚዎች ዳታ ቤዝ በደበብ፣ ደ/ምስራቅ ያለ ሳምረ፣ በምስራቅ በሁሉም ወረዳዎች የነበረ መሆኑና ፔሮል ያዘጋጁ መሆናቸው፣ በማእከላይና ሰ/ምዕራብ ዞኖች ያሉ ወረዳዎች ግን ዳታ ቤዝ ከመያዝና ፔሮል ከማዘጋጀት ሰፊ ክፍተት መኖሩ
- በአብዛኞቹ ወረዳዎች የሴፍትነት ተጠቃሚዎች የሴፍትነት በጀት አልተላከልንም በማለት እርዳታ እያገኙ አለመሆኑና እርዳታ በሚሰጡ ወረዳዎች ደግሞ ከአምስት ቤተሰብ በላይ ያላቸው መመርያው አይፈቅድም በማለት እየከለከሏቸው መሆኑበቀጣይ በጀት ቢመደብለት
- የሚሰጠው እርዳታ ሙሉ ፓኬጅ አለ መሆኑ የአልሚ ምግቦች እጥረት መኖሩን

- የሚደረግ ርዳታ ከጥናት የተነሳ ሲሆን ከዞን በወረደ ኮታ መሰረት መሁኑ /ደቡብ ምስራቅ/
- በየአከባቢው የነበሩ መጋዝኖች በጦርነቱ ምክንያት ጥቃት ስለደረሰበት ለአገልግሎት የተመቻቹ አለመሆኑ በተለይም ብክ/አውላዕሎና ራያ ዓዘቦ ከፍተኛ ጥቃት ደርሶባቸዋል፣ የመጋዝኖች ጠባቂ/ዘበኛ ባለመኖሩና ያላቸው ደግሞ መጠበቅያ መሳርያ ባለመኖራቸው ለሚላከው ርዳታ ደህንነት አስቸጋሪ እንዳደረገው
- የሚሰጠው እርዳታ ለሁሉም ተደራሽ አለመሆኑና የሚሰጠው መጠን ከአከባቢ ወደ አከባቢ ትልቅ ልዩነት ያለ መሆኑና ለአንድ ቤተሰብ እስከ 2.5 ኪ/ግ ስንዴ ለወር እየተሰጠ መሆኑ
- በተለያዩ ወረዳዎች የተለያየ የህል ዕደላ አሰራር መኖሩን ለአብነት የማረት ወረዳዎች የሁለት ወር ሲሰጣቸው የመንግስት የአንድ ወር እየተሰጣቸው መሆኑን እንዲሁም የዕለት ደራሽ እርዳታውና የሴፍቲኔት እርዳታው በፔሮል ለመስጠት የሚነሱ ያለመግባባቶች አሉ ከአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ጋር ልዩነት መኖሩን

6. በየደረጃው የፈረሱና የተዘረፉ የመንግስታዊ ተቋማት እና የተበተነውን የሰው ሀይል ፈጥኖ መልሶ ማደራጀትና ወደ ስራ ማሰማራት፡፡

- ✓ እስካሁን በተረጋገጠው በሁለት ወረዳዎች ሁለት ባለሞያዎች ብጦርነቱ ምክንያት ሞቷልፍተኛ በተደረገባቸው ወረዳዎች ብቻ ነው ይህ ቁጥር ሊጨምር ይችላል
- ✓ ሁሉም ሰራተኛ ወደየመስራቤቱ እየሄደ ሪፖርት አድርጓል
- ✓ ደሞዝ በተመለከተ በሁሉም ወረዳዎች እየተከፈለ ሲሆን ጥልቅ ክፍተት የነበረበት በማእከላይ ዞን ግን በጣም ዘግይቶ የተከፈለ ሲሆን ግዝያዊመስተዳድር የሌላቸው ወረዳዎች እስከ ቅርብ ግዜ ያልከፈሉ ወረዳዎች መኖራቸው፣ ደሞዝመከፈሉብለሞያዎች ሃላፊነት እንዲሰማቸውና በተወሰነ መልኩ ወደ ስራ እንዲገቡ ችለዋል
- ✓ ይሁን እንጂ በሁሉም አከባቢ የሚገኙ ቀበሌዎች የተሟላ ሰላም አለመኖሩ፣ የትራንስፖርት እጥረትና ስራማስኬጃ አለመኖሩ ወደስራ መግባት አስቸጋሪ አድርጎታል

ትግራይ ክልላዊ መንግስት ቢሮ ልምዓት ሕርሻን ገጠርን
The National Regional State of Tigray Bureau Of Agriculture & Rural Development

- ✓ በየደረጃው የወደሙና የተሰረቁ ንብረቶች ኢንቨንተሪ አልተጀመረም ነበር አሁን ግን የኢንቨንተሪ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ስራ ገብቷል፡፡

  - ያለ እ/አላጀናእንደርታ ወረዳዎች ሌሎች  የሌለች ወረዳዎች የግብርናና ገጠር ፅህፈት ቤቶች ተዘርፈል፣ አሁን ሰራተኞች ቁጭ ሚሉበት፣የሚፅፉበት፣ የሚያትሙበት ዕድል የላቸውም

  - በሁሉምወረዳዎች ከአንድ እስከ ሶስት መኪኖች ተዘርፏል፣ ሞተር ሳክሎችም ተዘርፏል፣ በዚሁም መሰረት ወደ ቀበሌ ወርዶ ለመደገፍ ተቸግሯል

  - በየአከባቢው ያሉ የእንስሳሕክምናክሊኒኮችኣብዛኞቹ ተዘርፏል

  - በየወረዳው ብዛት ያላቸው የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከላት ተዘርፏል /ኤሌክትሮኒክስና ሌሎች ንብረቶች/

  - ኣሁንም ያለተዘረፉና ለሚገዙ ንብረቶች ዘበኛ ባለመኖራቸውን ዘበኛ ባለባቸም ትጥቅ ባለሞኖራቸው ዋስትና የላቸውም

  - የእንስሳት ስርቆት ከቅያቸው በሻእብያ ሰራዊት በመኪና እየተጫኑ ተወስዷል ኣሁንም እየተወሰዱ ናቸው

  - በየአከባቢው የወደሙ የመስኖ መሰረተ ልማቶች እንዳሉ የገለፅሉን ሲሆን ዝርዝሩ ግን በጥናት የሚመለስ ይሆናል

  - በራያዓዘቦየተሰማሩ ሰብሣብቶች ንብረታቸውና መሰረተ ልማቶች ወድመዋል

- ✓ ኣብዛኞች ወረዳዎች በቂም ባይሆን ለመስኖ ማዳበርያ በማጋዝናቸው የነበራቸው ለኣርሶ ኣደር ማደል የጀመሩ እ/ኣላጀ፣ እ/መኾኒ፣ ላ/ማይጨውን፣ ክልተ አውላዕሎ፣ እንደርታ፣ ሕንጣሎ ሲሆኑ የቀሩ ወረዳዎች ግን ማደል ኣልጀመሩም፡፡ እዚህ የሚነሱ ጥያቄዎች የማዳበርያ ሽያጭ ገቢ የሚሆንበት የባንክ ኣካውንት ዝግ ስለ ሆነ ወዴት እሳንገባዋለን? የሸጥነው ገንዘብ እንዳንዘረፍ ምን ዋስትና ኣለን? ኣዲስ ለሚመጣው ማዳበርያ እንዳይዘረፍ ምን ዋስትና ኣለን? የሚሉ ይገኙበታል፡፡

- ✓ የተባዛ ምርጥ ዘር በሁሉም ወረዳዎች መሰብሰብ አልጀመሩም፡፡ ስለዚህ አሁንም ከብዜት ማህበራትን ከአዞች አርሶ አደሮች ያላቸውን ዘር ለማህበር እንዲያስረክቡ መረዳዳት የተቻለ ሲሆን ዘር የመገኘቱ ዕድል ግን በጣም አነስተኛ መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም የተሰበሰበ ዘር ማን ይጠብቀዋል የሚል ትልቅ ስጋት አለ፡፡ ገንዘብ ለማውጣት የባንክ ጣራ ደግሞ ለዚሁ አመቺ አይደለም የሚሉ ጥያቄዎች አንስተዋል፡፡

- ✓ በጥቅሉ ስለ ግብአት ፍላጎታቸው እያንዳንዱ ወረዳ ወደ ክልል እንዲጠይቅና የጥብቃ ስራ ደግሞ በየወረዳው ያሉ ኮማንፖስት መፍታት እንደሚችሉ ተረዳድተናል

- ✓ ሁሉም ድጋፍ ያገኙ ወረዳዎች በእርዳት ላይ ብግብርና ፅ/ት ቤት ማነጅመንት እየገመገሙና እየደ ገፉ እንዳሉ መገንዘብ ችለናል

- ✓ ይሁን እንጂ እርሶ አደሩ የመስኖና የእንስሳ ልማት ስራዎች እየሰራ ቢሆንም ከፍተኛ የግብአት እጥረት ግን አጋጥሞታል / ማዳበርያ፣ የእንስሳ መድሃኒቶች፣ ም/ዘር ወዘተ../ በተጨማሪም የባለሞያ ድጋፍ ገና ያልጀመረ መሆኑ ማረጋገጠጥ ተህኋል፡፡

- ✓ በዚህ መሰረት ሁሉም ባለሞያ ሞያዊ ድጋፍ የሚሰጥበት ሁኔታ እንዲመቻችና ባጅ ወጥቶላቸው በኮማንፖስት እውቅና እንዲንቀሳቀሱ ተረዳድተው እንዲሰሩ እየተደረገ ነው፡፡

- ✓ የደን ውድመት በተመለከተ የኤሌክትሪክ መብራት ባለመኖሩ ምክንያት በየአከባቢው እየወደመ መሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡ የደን ጥባቂዎች ደሞዝ ስላልተከፈሉና የመጠበቅያ ትጥቅ ስለሌላቸው ጥበቃው ለማጠናከር አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ የድጋፍ ቡዱኑ በየወረዳው ባሉ ኮማንድፖስት መረዳዳት በማድረግ ጠባቂዎች ትጥቅ እንዲሰጣቸው፣ በእ/አላጀ እርዳታ በመስጠት ጥበቃውን እንዲጠናከር ያደረጉ ሲሆን ሌሎች ወረዳዎች ደግሞ ይህ እንደ መፍትሄ እንዲያደርጉት አቅጣጫ የሰጠ ሲሆን በክልል ኮማንድ ፖስት ደግሞ አቅጣጫ ማውረድ እንዳለበት ለማስገንዘብ እንወዳለን፡፡

- ✓ የፍራፍሬ፣ የደንናየመኖ ችግኝ ጣብያዎች ስራ በኣብዛኛው የቆመ ሲሆን በኣንድ ኣንድ ኣከባቢ ግን በስራ ላይ ይገኛሉ ለምሳሌ ብእ/ኣላጀ፣ እ/መሆኒ፣ ኣፅቢ ውዘተ... ይሁን እንጂ ኣሁንም ከሓምሌ ወር ጀምሮ ደሞዝ ባለመከፈሉ ስራውን ለማስቀጠልና ለማስጀመር ኣስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ የደሞዝ ጉዳይ ባስቸኳይ በክልል መፈታት ያለበት ሁኔታ ነው፡፡

- ✓ ለእንስሳት ቀለብ የሚውል የሰብል ተረፈ ምርት በደቡብና ደ/ምስራቅ ወረዳዎች በተሻለ መጠን መሰብሰብ የተሞከረ ሲሆን በምስራቃዊና ማእከላዊ ዞኖች ያሉ ወረዳዎች ግን በማሳው ሳለ እና በቤትም በኤትራ ሰራዊት የተቃጠለና የተዘረፈ ሞሆኑና ከፍተኛ የቀለብ እጥረት መኖሩ መገንዘብ ችለናል፡፡ ካሁን ጀምሮ በለስ መመገብ ጀምሯል፡፡ በደቡብና ደ/ምስራቅም ቢሆን ተጨማሪ የእንስሳት መኖ እንደሚያስፈልግና በየወረዳው ከሚገኙ መኖ ኣቅራቢዎች ማህበራት፣ ግለሰዎችና ኢንዳስትሪዎች በመነጋገር መፍታት እንዳለበት ኣቅጣጫ የተሰጠ ሲሆን በክልል በኩልም ትልቅ ስራ እንደሚያስፈልግ ተገንዝበናል፡፡

- ✓ በኣንድ ሁለት ወረዳዎች የ FMD እየተከሰተባቸው መሆኑም ኣረጋግጠናል (ወረዳ ክ/ኣዉላዕሎ፣ ሳምረ)

## 7. በኣጠቃላይ በትግራይ ክልል በተከሰተው ጦርነት የደረሰው ጥቃት

### 7.1. በትግራይ ህዝብ ደረሰው ሰውኣዊ ቀውሶች

- ✓ በኣጠቃላይ ኣሁን ከ95% በላይ የትግራይ ህዝብ ንብረቱና ሃብቱ በመወሰዱ ኣልያም ገቢ የሚያኝባቸው የስራ መስኮች ስራ በማቆማቸው ተረጂ እንዳደረገውና የዕለት ምግብ ድጋፍ የሚያስፈልገው መሆኑ

- ✓ የንብረትና የሃብት ዘረፋውና ንፁሃን ዜጎች በየጎደናው መግደልና ቤቶች ማቃጠል ኣሁንም እየቀጠለ መሆኑ

### 7.2. በግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ስራዎችና ተቅዋማት የደረሱ ጥቃቶች

#### 7.2.1. በሰብልና ሆርቲካልቸር ልማት የደረሱ ጥቃቶች

- ✓ ከ95% የትግራይ ኣርሶ ኣደር የግብርና ግብኣቶች ማለትም ማዳበርያ፣ ምርጥ ዘርና የሰብል ጥበቃ ኬሚካሎች መግዛት ኣይችልም

- ✓ በብዜት የነበሩ መርጥ ዘሮች ባለመሰብሰባቸው በክልሉ ምንም ምርጥ ዘር የለም
- ✓ ከ30% በላይ መስኖ ተጠቃሚዎች የግብርና ግብአቶች ማለትም ማዳበርያ፣ ምርጥ ዘርና የሰብል ጥበቃ ኬሚካሎች መግዛት አይችልም
- ✓ ከ10% በላይ የአርሶ አደሩ የመስኖ አውታሮች እንዲሁም 90% በላይ የባለሃብት የመስኖ አውታሮችን በጦርነቱና በወራሪው ሃይል ወድሟል፡፡
- ✓ ከ70% በላይ የፍራፍሬ፣ መኖና ደን ችግኝ ጣብያዎች ንብረቶች መወረራቸውና ለአርሶ አደሩ ችግኝ ለማቅረብ የማይችሉበት ደረጃ ደርሷል
- ✓ ከ80% በላይ የእንስሳት ጤና ጣብያዎች በተወሰነ መልኩ ህንፃቸው ምሉ በምሉ ደግሞ በውስጣቸው የሚገኙ መድሃኒቶችና የጤና ጣብያ መሳርያዎች ተዘርፏል

7.2.2. በእንስሳት ሃብት ልማት የደረሱ ጥቃቶች

- ✓ ከ70% የእንስሳት መኖ በጦርነቱ ምክንያት ዕጥረት አጋጥሟቸዋል፣ 65% የእንስሳት መኖ መቀነባበርያዎች ተዘርፏል ተሰባብረዋል፣ 28 የዱቄትና ቅባት ወፍጪዎች፣ ሱካርና የቢራ መጥመቅያ ፋብሪካዎች፣ ማረጃ ና ሌሎች ተዘርፈዋል ለብልሽት ተዳርጓል
- ✓ ሁሉም የእንስሳት ማሻሻያ ማእከላትና ስራዎቻቸው ተቋርጧል
- ✓ ሁሉም የደሮ አርቢዎች /out-growers/ ስራቸው ተቋርጧል,
- ✓ ሁሉም (85) የወተት ማጠራቀምያና ማቀነባበርያ ማእከላት ተዘርፏ/ወድሟል
- ✓ ከ75% በላይ እንስሶች በወራሪው ሃይል ታርዷል፣ ተዘርፏል፣ ተሰዷል
- ✓ በጦርኖቱ ምክንያት ንቦች ከቆፋቸው ወጥተው ተሰዷል
- ✓ የሰብልና የእንስሳት ምርታማነት ክፉኛ ተጎድቷል
- ✓ የእንስሳት፣ የሰብልና የሆርቲካልቸር ምርቶች ገበያ ክፉኛ ተጎድታል

#### 7.2.3. በተፈጥሮ ሃብት ልማት የደረሱ ጥቃቶች

- ✓ በክክልሉ የተሰሩ ተፋሰሶችን የለሙና የተጠበቁ የደን መሬቶች የጦርነት አውድማ ሁነዋል ፣ የውስጥ ህጋቸው ተጥሰዋል ፣ ልቅ ግጦሽ ተባራክተዋል ፣ የደን ጭፍጨፋ በስፋት አለ ፣ ጠባቂዎች ጠመንጃቸው ተነጥቀዋል በተፈጥሮ ሃብት በተካሄደው ጥናት እስካሁን ከ18.5 ቢሊዮን ብር በላይ የህዝብ ጉልበት የወጣበት ተፈጥሮ ሃብት ስራዎች ወድመዋል ይህ ጥናት በቀጣይ የሚጠናከር ይሆናል
- ✓ 10 %የመንግስት ደኖች የውስጥ ህጋቸው ተጥሰዋል
- ✓ ከ90% በላይ ተፋሰሶች የውስጥ ኣሰራራቸው ተጥሰዋል ለልቅ ግጦሽ ተዳርገዋል
- ✓ ሁሉም የመንግስታዊና የህብረተሰቡ ደኖች ወደሚል፣ ያለጠባቂ ቀርቷል፣ የዱር ኣራዊቶች ተሰዷል

#### 7.2.4. በግብርናና ገጠር ልማት ጽህፈት ቤቶች የደረሰ ጥቃት

- ✓ የጥቃት መጠኑ የተለያየ ቢሆንም 100% የግብርና ፅህፈት ቤቶች ከፅህፈት መሳርያዎች እስከ የትራንስፖርት መኪኖችና ሞተሮች መወረራቸውና ስራ ላማስጀመር ኣስቸጋሪ ኣድርጎት እንዳለ
- ✓ ከ50% በላይ የኣርሶ ኣደሩ ማሰልጠኛ ማእከላት ንብረቶች ተወረዋል

## 8. የትግራይ ክልል ኅብረት ሥራ ማኅበራት ወቅታዊ ሁኔታ የተመለከተ ሪፖርት

በትግራይ ክልል ጦርነት ከመካሄዱ በፊት የክልላችን ኅብረት ሥራ ማኅበራት ገጠርና ከተማ በገበያ በማስተሳሰር ለአባላቸውና አባል ላልሆኑ የአካባቢያቸው ህብረተሰብ ምግብና ምግብ ነክ አቅርቦቶችን በሚፈለገው ደረጃ በማቅረብ፣ የግብርና ግብዓቶች በማቅረብና በማከፋፈል፣ በምርት ማቀነባበርና አግሮ-ሚካናይዜሽን ስራ በመሰማራት፣ የህብረተሰቡ የቁጠባ ባህል እንዲያድግ በማድረግ በኢንቨስትመንት ስራ በመሠማራት በኢኮኖሚው ወሳኝና ተኪ የሌለው ሚና ሲጫወቱ ነበር። ስለሆነም 5,204 መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ 75 ዩኔኖች፣ 1 ፌደሬሽን በድምሩ 5,280 ህብረት ሥራ ማህበራት በማደራጀት ብር 3,759,818,318 ንፁህ ካፒታል በመያዝ 1,387,194 አባላት ተጠቃሚ በማድረግ ላይ

ነበሩ። ይሁን እንጂ በአሁን ግዜ ለህብረተሰቡ ሲሰጡት የነበረ መጠነ ሰፊ አገልግልት በክልላችን በተፈጠረው ጦርነት ሳቢያ በንብረታቸውና የሰው ኃይላቸው ላይ ከፍተኛ ውድመትና ዝርፍያ በመድረሱ ምክንያት የሚሰጡት አገልግሎት እንዲገታ ሆኗል። ስለሆነም በክልሉ ያሉት ኅብረት ሥራ ማኅበራት እስከ አሁን ባለው ሁኔታ ያሉበት ደረጃ በተወሰነ መልኩ ለማሳየት ሪፖርቱ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

**የኤጀንሲው ሰራተኞች፣ የህብረት ሥራ አመራሩና ቅጥር ሰራተኞች ስራ መጀመርን በተመለከተ**

- ከክልል እስከ ወረዳ ያሉት የኤጀንሲ ሰራተኞች ከ97% በላይ በመደበኛ ስራቸው ተገኝተው ሪፖርት በማድረግ ስራ ጀምሯል። ይሁን እንጂ በምዕራብ ዞን የነበሩት ባለሞያዎች በሥራ ቦታቸው የሉም
- ስራ መጀመር ከነበረባቸው የህብረት ስራ አመራሮች ውስጥ ስራ ላይ ያሉ ከ60% አይበልጡም። የቀሩት አመራሮች ግና የት እንዳሉ አይታወቅም
- ስራ መጀመር ከነበረባቸው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ቅጥር ሰራተኞች ውስጥ ወደ ሥራ የተመለሱ 80% ገደማ ናቸው  የቀሩት ቅጥር ሰራተኞች ግና የት እንዳሉ አይታወቅም
- አሁን ባለው ሁኔታ የህብረት ሥራ ማህበራቱ ስራ እንቅስቃሴ በመዳከሙ ምክንያት ምንም ገቢ ስለሌላቸው የሰራተኞች ቅነሳ ጀምሯል ለምሰሌ ቦኽራ ሁለ ገብ ዩኔን 20 ቅጥር ሰራተኞች ከሥራ ገበታቸው አሰናብቷል

**የግብዓት ፍላጎት በተመለከተ**

- በክልሉ በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት ለአርሶ አደሩ የምርጥ ዘር አቅርቦት በበቂ ሁኔታ ሲያቀርቡ የነበሩ 2 ዩኔኖችና 87 መሰረታዊ ምርጥ ዘር ብዜት ህብረት ስራ ማህበራት በተፈጠረው ሁኔታ ከፍተኛ ዝርፍያና ዉድመት ስለ ደረሳቸው ስራቸውን አቁመዋል። ስለሆነም በአሁን ግዜ 492,000 ኩ/ል ምርጥ ዘር ለ2013/14 ምርት ዘመን  ለክልሉ እንደሚያስፈልግ ማወቅ ተችሏል
- በተመሳሳይ መልኩ የአፈር ማዳበርያ 800,000 ኩ/ል ለ2013/14 ምርት ዘመን ያስፈልጋል

**የደረሰ ጉዳት በተመለከተ**

እንደሚታወቀው ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከፖለቲካ፣ ከዘር፣ ከሃይማኖትና ሌሎች ልዩነቶች ነፃና ገለልተኛ ተቋማት ናቸው። ይሁን እንጂ ህብረት ሥራ ማህበራት እንደ ተቋም

ሃብታቸውና ንብረታቸው ተዘርፋል ወድሟል፣ አመራራቸውና ቅጥር ሰራተኞች የተገደሉም አሉ ለምሳሌ በእምባ አላጀ ወረዳ። እንዲሁም በመአዲ ክ/አውላዕሎ ሁ/ገብ ዩኔን የ36.6 ሚልዮን ብር ግምት ያለው ንብረት፣ በሓድነት ራያ የዘር ብዜት ዩኔን በአጠቃላይ ግምታቸው ከ21.6 ሚልየን ብር የሚሆን የተለያዩ ንብረቶች፣ በወልዋሎ ሁ/ገብ ዩኔን 100% ንብረቱ፣ በዓጋመ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኔን 100% ንብረቱ፣ በስምረት ሁ/ገብ ዩኔን 100% ንብረቱ፣ ሰየምቲ ሁ/ገብ ዩኔን 100% ንብረቱ፣ በአድያቦ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኔን 100% ንብረቱ፣ ተመስገን ሁ/ገብ ዩኔን 100% ንብረቱ፣ በንግስቲ ማክዳ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኔን 100% ንብረቱ፣ ሐወልቲ ሁ/ገብ ዩኔን 100% ንብረቱ በአጠቃላይ በክልሉ ስፍር ቁጥር የሌለው ንብረት በወራሪዎች ተዘርፏል፣ ወድሟል። በተጨማሪም በክልሉ የሚገኙት 994 የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት 98% በተፈጠረው ቀውስ ምክንያት ስራቸውን አቁሟል። ለግብዓት ስርጭት አገልግሎት ይውሉ የነበሩ 515 ፓወር ባንክ፣ 60 ሶላር ቻርጀር፣ 33 CDMAና 9 የዳታ ሰርቨሮች ተዘርፏል ከጥቅም ውጪ ተደርጓል።

**ተሽከርካሪዎች (መኪናዎች) በተመለከተ**

- ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት የህብረት ሥራ ማህበራት የጭነት መኪኖች (አይሱዙ፣ ኤፍኤስአር፣ ሲኖ ትራክና ተሳቢ) 42 መኪኖች የነበሩ ሲሆን እስከ አሁን ባለው መረጃ 34 መኪኖች በተለያዩ ኃይሎች ተወስደዋል
- ኅብረት ሥራ ማኅበራት አርሶአደሩ የሜካናይዜሽን ተጠቃሚ እንዲሆን 50 ትራክተሮች በኅብረት ሥራ ማህበራት ተገዝተው አገልግሎት እየሰጡ ነበር። ይሁን እንጂ ከነዚህ ትራክተሮች ከግማሽ በላይ የሚሆኑትን በተለያዩ ኃይሎች ተወስደዋል

**አግሮ-ፕሮሰሲንግ ፋብሪካዎችን በተመለከተ**

የክልላችን ህብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ ፋብሪካዎች በመገንባት ለአባላትና ለውጪ ገበያ የሚውሉ ምርቶች እሴት በመጨመር የውጪ ምንዛሪ በማስገኘት ረገድ ትልቅ ሚና ነበራቸው

- 3 ሰሊጥ መፈልፈያና ማጣርያ ፋብሪካዎች ነበሩ። ሁሉም ዝርፍያና ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባችዋል
- 2 የማር ማጣርያ ፋብሪካዎች ነበሩ። ሁሉም ዝርፍያና ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባችዋል
- 11 የእንስሳት መኖ ማቀነባበርያ ፋብሪካዎች ነበሩ። በ7ቱ ዝርፍያና ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባችዋል

- 3 የወተት ማቀነባበርያ ፋብሪካዎች ነበሩ። በ2ቱ ዝርፍያና ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባችዋል
- ሩዝና በቀሎ መፈልፍያ 14 ነበሩ። በምን ሁኔታ እንዳሉ አይታወቅም

በቢሮ እቃዎችን የደረሰ ዝርፍያ በተመለከተ

| ተ/ቁ | የተዘረፉ የንብረት ዓይነቶች | የወረዳ ኅብረት ሥራ ጽ/ቤት | የ75 ዩኔን ኅብረት ሥራ ማኅበራት |
|---|---|---|---|
| 1 | ኮምፒተር | 525 | 450 |
| 2 | ፕሪንተር | 350 | 150 |
| 3 | ፎቶ ኮፒ ማሽን | 35 | 75 |
| 4 | ላፕ ቶፕ | 70 | 100 |
| 5 | ቢመር | 35 | 75 |
| 6 | ጠረጴዛ | 525 | 500 |
| 7 | ወንበር | 525 | 750 |

NB.

1. የወረዳ ጽ/ቤት ንብረት 98% ተዘርፏል፣ ተቃጥለዋል
2. የዩኔን ኅብረት ሥራ ማኅበራት 95% ተዘርፏል፣ ተቃጥለዋል
3. ከግማሽ በላይ የወረዳና የኅብረት ሥራ ማኅበራት መዛግብትና ሰነዶች ከጥቅም ውጪ ተደርጓል ተቃጥለዋል

የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ የፋይናንስ አቅም በተመለከተ

- በመስክ ዳሰሳ ለመረዳት እንደተቻለው በኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር እጅ የነበረ ጥሬ ገንዘብ በሌባና ቀማኛ እንደተወሰደ በተለያዩ ባንኮች የነበረ ገንዘባቸው ግና ችግር እንዳልደረሰው መገንዘብ የቻልን መሆኑ። ይሁን እንጂ የአብዛኞቹ መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማኅበራትና አንዳንድ ዩኔኖች ሒሳብ በደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ በመሆኑ ደደቢትም እንደተቋም ሒሳብ እንዳያንቀሳቅስ በመታገዱ ምክንያት ማኅበራቱ አገልግሎት ለመስጠት መቸገራቸውን ታውቀዋል።

መልካም ተመኩሮ

- በአስቸጋሪው የጸጥታ ችግርም ሆኖው ኅብረት ስራ ማህበራቱ ለህዝቡ ያለማቋረጥ አገልግሎት መስጠት የቀጠሉበት ሁኔታ መኖሩ በተለይም በመቐለ ከተማ ያሉት ሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት። በተጨማሪም የኅብረት ስራ ማህበሩ ሀብትና የቀበሌ ንብረትም እንዳይዘረፍ ከፍተኛ ጥበቃ ሲያደርጉ የነበሩ ማኅበራት በመቐለ ከተማ መኖራቸው

The National Regional State of Tigray Bureau Of Agriculture & Rural Development

- ለመስኖ የሚውል ግብዓት (ማዳበርያ) በማህበራቱ እንዲሰራጭ ጥረት ያደረጉ ዩኔኖች መኖራቸው (ለምሳሌ:-መአዲ ክልተ አውላዕሎ፣ እንደርታ፣ ዓዲ ጉደም፣ አላጀ፣ ቦ'ክራ ዩኔኖች)

**ትኩረት የሚሹ ማነቆዎችና መፍትሔዎቻቸው**

- የህብረት ስራ ማህበራት ብዙ ሃብት የሚያንቀሳቅሱ የህዝብ ተቋማት ስለሆኑ የክልሉና የዞኑ ኮማንድ ፖስት ችግሩን በጥልቀት በመረዳት ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚቻልበትን መንገድ ማመቻቸት ቢቻል (የማህበራት ጥበቃ ሰራተኞች መሳሪያ ማስታጠቅ የሚቻልበት ሁኔታ ቢፈጠር)፣ ህዝብና አባላቱም ከኮማንድ ፖስቱ ጋር በመቀናጀት ንብረታቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው የግንዘቤ መድረክ ቢዘጋጅ
- አብዛኞቹ በተለይም የገጠር ኅብረት ሥራ ማኅበራት ሒሳብ በደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ የሚገለገሉ ስለሆነ የክልል ግዝያዊ መስተዳድሩ ከፌደራል መንግስት ጋር በመቀናጀት የደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ ሥራ የሚጀምርበትን ሁኔታ ቢያመቻች
- በክልሉ በተፈጠረው ማህበራዊና ኢኮኖምያዊ ቀውስ ኅብረት ሥራ ማኅበራቱ በቋሚ፣ በተንቀሳቃሽ እንዲሁም በፋብሪካዎቻቸው ጉዳት በመድረሱ፣ ህብረተሰቡ ከደረሰበት ቀውስ የተነሳ የመቆጠብ አቅሙ በመዳከሙ፣ የብድር አቅርቦት የሚሰጡ ማይክሮ ፋይናንሶች አገልግሎት መስጠት ከማቆማቸው የተነሳ ከፍተኛ የሆነ የፋይናንስ አቅርቦት ችግር ታይቷል። ስለሆነም የፋይናንስ አቅርቦት የሚመቻችበት ሁኔታ ቢፈጠር (ለምሳሌ ግብአት፣ ምግብ ነክና ምግብ ነክ ያልሆኑ አቅርቦቶች በብድር ማቅረብ ቢቻልና ፋብሪካዎቻቸው በፍጥነት ተጠግነው ሥራ ቢጀምሩ)። በተመሳሳይ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት በማጠናከር ወደ ቀድሞ መደበኛ ስራቸው እንዲመለሱ ሥራ ቢሰራ
- በክልሉ ወጥ የሆነ የግብዓት ስርጭት እና የግብዓት ሽያጭ፣ ከብድር የተሰበሰበ የገንዘብ ዝውውርን በተመለከተ በከፍተኛ የክልሉ የኮማንድ ፖስት አባላት፣ በህብረት ስራ ማሕበራት አመራር አካላት፣ በህብረት ስራ ኤጀንሲ ባለሞያዎችና ባንኮች መካከል የመግባቢያ መድረክ ቢመቻች፣
- ገንዘቡን ለሚያንቀሳቅሱ የማህበራቱ ገንዘብ ያገዦች በቀማኛና ሌቦች ጥቃት እንዳይደርስባቸው አስፈላጊው ጥበቃ ቢደረግላቸው
- በቢሄራዊ ባንክ ገንዘብ ለማውጣት በተጣለው ገደብ ምክንያት ህብረት ስራ ማህበራቱ በእንቅስቃስያቸው ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ በመሆኑ በተለያዩ ባንኮች

መካከል ከሒሳብ ወደ ሒሳብ ለማዘዋወር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት ቢቻል አልያም ገደቡ ማንሳት የሚቻልበት ሁኔታ ቢፈጠር

- በክልሉ በተፈጠረው ማህበራዊና ኢኮኖምያዊ ቀውስ ከፍተኛ የሃብትና ንብረት ውድመት በመድረሱ የፌደራል ተቋማት ከክልል እስከ ቀበሌ ላሉት መዋቅሮቻቸው አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ መልሶ የማደራጀት ስራ በትጋት ቢሰራ። ለምሳሌ:- የጽ/ቤት መገልገያ ማሟላት፣ በሎጂስቲክና ስራ ማስኬጃ ድጋፍ፣የተደራጀ የባለሞያ ድጋፍ፣ የተለያዩ ሞያዊ ስልጠናና ማነቃቅያ መድረኮችን መፍጠር ቢቻል፣ ህብረት ሥራ ማህበራት መልሶ ለማቋቋም እና ድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ ቢዋቀር
- አጠቃላይ የመንግስትና ህዝብ አገልግሎት ለመስጠት ተደራሽ ባልሆኑ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ተደራሽ ለማድረግ ፌደራልና ክልል በመቀናጀት አፋጣን መፍትሔ ቢያስቀምጡ

## 9. በክልልና በፌደራል ትኩረት ተሰጥቷቸው መሰራት ያለባቸው

- ✓ የግብርና ስራው ለማስጀመርና ባለሞያ ለአርሶ አደሩ እስከ ቀበሌ ወርዶ ለመደገፍ በሁሉም አከባቢ ፀጥታ ማስከበር የመጀመርያ ጉዳይ መሆኑ
- ✓ የኤርትራና የአማራ ሰራዊት ከትግራይ መውጣት እንዳለበት ካለሆነ ማልማትም ሆነእርዳታ ማዳረስ እንደማይቻል
- ✓ በPSNP 4-ለክልሉ ተመድቦ የነበረ በጀት ሁሉም መለቀቅ አለበት የተጠቃሚዎችና የተለያዩ የተፈጥሮ ሃብት ስራዎች ያልተከፈለ በጀት ያለ ስለ መሆኑ፣
- ✓ የሬድኤት ጉዳይ ለሁሉም ለማዳረስ በግዜ፣ በመጠንና ፍትሃውነት መታየት እንዳለበትና በየደረጃው ያሉ አመራሮች በዚህ ትኩረት አድርገው መስራት አለባቸው
- ✓ ግዝያዊአስተዳደር የሌለባቸው በፍጥነት እንዲኖራቸው ማድረግና ወደ ስራ ማስገባት ይገባል
- ✓ በተቅዋማት ላይ የደረሰ ጥቃት ስራ የሚያስጀምር ድጋፍ መደረግ አለበት

- ✓ የግብርና ግብኣቶች ማለትም ማዳባርያ፣ም/ዘር፣የሰብልና የእንስሳት መድሃኒቶችና የመርጫ መሳርያዎችና ሌሎች ቁሳቁሶች በተለይም የማዳበርያና የእንስሳት መድሃኒት በኣፋጣኝ መቅረብ ይኖርበታል፣ ለኣርሶ ኣደሩ በነፃ ድጋፍ መሰጠት ይኖርበታል
- ✓ በየቀበሌውና ወረዳዎች ያሉ ህ/ስ/ማሕበራት ለኣርሶ ኣደሩ ድጋፍ እንዲሰጡ ሰፊ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሰፊ ድጋፍ ማድረግ ይጠይቃል
- ✓ በፌደራል የሴፍትኔት በጀት ወደ ክልል በኣፋጣኝ መላክ እንዳላበትና እርዳታው የሚሰጥበትን ግዥዎች እንዲከናወኑ ያስፈልጋል ኣሰራሩ ደግሞ በፅሁፍ የሚወርድበት ሁኔታ ቢፈጠር